# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ታኅሣሥ 8 ቀን 2008 ዓ.ም.

## የሕዝብን ተቃውሞ ማፈን ቀውስን አያስወግድም

ባለፉት ጥቂት ቀናት የወያኔን የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ሲቃወሙ የነበሩ በርካታ ዜጎችን ወያኔ በግፍ ጨፍጭፏል። ኢሕአፓ አምባገነኑ የወያኔ ቡድን በዜጎች ላይ ያካሄደውን አረመኔያዊ ድርጊት እየኮነነና እያወገዘ ይህን አጥፊ ቡድን ለማስወገድ የሚካሄደው ትግል አገራዊ መልክ ይዞ ተጠናክሮ እንዲፋፋም ጥሪውን ያስተላልፋል።

ኢሕአፓ በልዩ ልዩ ከተሞች ተማሪው፤ በተለይም ስቃይና መከራው ያንገፈገፈው የሕዝብ ክፍል ሲያካሂደው የነበረውን ተቃውሞና ጸረ ወያኔ ትግል ደግፎ፤ የተሰዉትን ዜጎችንም አክብሮና ዘክሮ ወያኔን ከጥፋቱ በዚህ መንገድ ሊያመልጥ እንደማይችልም ሲያሳስብ ቆይቷል ። በተጨማሪም ይህን የሕዝብ ትግል በጽንፈኛ አቅዋማቸው ከሕዝብ ተገልለው የቆዩ ሰለባ ሊያደርጉት፤ሊጠቅሙበትና፤የደገፉ መስለው ክንድና አቅም ሊያሳጡት ከየስርቻቸው ብቅ ያሉትን አስመሳዮችና የወያኔ ቅጥረኞችንም በሙሉ አውግዞ ሕዝብ እንዲነቃባቸውም መክሯል፤ አሳስቧል።

ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ሕዝብን ከመሬቱ ሲያፈናቅል፤መሬት ሲቀማ፤ ሲያሳድድና በደል ሲያደርስ የቆየ ነው ። የሀገራችን የገጠር መሬት የአራሹ ማድረግን በመቃረን-- መሬት ለአራሹ የተባለውን በመጻረር-- ራሱን መንግሥት ብሎ መሬትንም የራሱ አድርጓል ። የወያኔ ባለስልጣኖች የአማራውንና የሌሎች ብሔረሰቦችን ወገኖች ከአንዳንድ ቦታዎች (ለምሳሌ ከጣና በለስ ከአርባጉጉ ከምስራቅ ወለጋ ውዘተ..) አፈናቅለውና አሰድደው መሬት አልባ ማድረጋቸውን በመቀጠል ወደ ጋምቤላም ተሻግረው መሬቱን ለባዕዳን ሸጠዋል። በሕገ ወያኔ የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት ነው ይባል እንጅ ሐቁ ሲነገር የወያኔ ነው ማለት ነው ።የቋራ ለም መሬት ለሱዳን ሲለገስ ጉዳዩ የኢትዮጵያ ማለትም የአገራችን ጉዳይ ሆኖ እያለና አጠቃላይ አገር አቀፍ ተቃውሞ ማስነሳት ሲገባው ተቃውሞውና እንቅስቃሴው ለአካባቢው ሰዎች ብቻ እንዲተው መደረጉ ትግሉ ጎልቶ እንዳይቀጥል እንቅፋት ሆኗል። በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባን ማስፋት በሚል ሽፋን ወያኔ ያቀደው የመሬት ዘረፋም አንድ ክልልን ወይም ብሔረሰብን የሚመለከት ሳይሆን የኢትዮጵያ ዜጎች የሆኑ አርሶ አደሮች መሬታቸውን በወያኔ ባለስልጣኖች ተቀምተው መናጢ ደሃ የሚሆኑበት፤ የወያኔ ባለስልጣኖችም የዘረፉትን መሬት በመሸጥ ሀብት የሚያካብቱበት ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ሊቆረቁር ሊያሳስብ፤ሊያስቆጣና ሊያነሳሳ የሚገባ ነው።። ። ወያኔ ጎንደርን ቆርሶና ቆራርሶ ወደ ትግራይ ጠቅልሎ አልጠግብ ባይም ሆኖ ይበለጥ ሊስፋፋ ሲጥር ተፈጥሮ ያለውንም ችግርና ግጭት መርሳት የሚቻል አይደለም ። በአጭሩ የወያኔ ዝርፊያ አንድ ክልልን ያጠቃ አይደለም--ሁሉንም በድሏል ፤እያሰቃየም ነው። የአዲስ አበባን የማስፋፋት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከረው የእነ ሰበታ፤ሰንዳፋ ወዘተ መሬትን እንዳደረገው እየቸበቸበ ለመክበር መሆኑ ክርክር አያሻውም ። የወያኔ ተለጣፊ ሆነው አምቦን የሚቦጠቡጡት ደግሞ በኦሮሞ ስም ተሰይመው ወንጀል ፈጻሚዎች ናቸውና ሌላ ጠንካራ ተቀናቃኝ እንዲመጣባቸው ስለማይሹ የራሳቸውን

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ተንኮል መሸረባቸው ከማንም ሊሰወር የሚችል አልሆነም ። በመሃልም በርካታ ኦሮሞዎች፤ አማሮች ወዘተ.. ሰለባ ሆነዋል፤አሁንም እየሆኑ ነው ።

የወያኔን አገዛዝ የምስረታ ሂደት ደግፈውና ጸረ አማራ ተልዕኮውን ተጋርተው የነበሩት መጨረሻቸው ምን እንደሆነ ሕዝብ የሚያውቀው መሆኑ እንዳለ ሆኖ ፀረ ሕዝቡ ወያኔ ይዞት የቆየው ፀረ ኦሮሞ አቅዋም ደግሞ የሚካድ አይደለም ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ሆነ ኢሕአፓ በኦሮሞዎች ሙሉ ተሳትፎ የታገለ መሆኑንም ታሪክ የሚያስታውሰው ነው ። በኢትዮጵያ የሕዝብ እኩልነት አልተረጋገጠም፤ የብሔር ብሔረሰብ ጭቆና አለ ብሎ በመናገሩም ሐቁ የማይዋጥላቸው ሁሉ እስካሁን ያወግዙታል። ጭቆናው ግን የነበረ መሆኑ ሀቅ ሲሆን በተለይም የኦሮሞ ሕዝብ እንደተቀረው ጭቁን ሕዝብ መሬቱና መብቱ ተቀምቶ በጢሰኝነት ይኖር እንደነበር የሚረሳ አይደለም ። ቀደም ብለው የነበሩ አገዛዞች ሕዝብን ሲጨቁኑ መቆየታቸው የማይካድ ቢሆንም ወያኔ ደግሞ ከሁሉም በተለየና በከረረ መልኩ ፀረ ሕዝብ ነውና በኦሮሞው ሕዝብ ላይ ኦሕዴድ የሚባል ተለጣፊ ቡድን ጭኖ፤ እስር ቤቶችን በኦሮሞዎች አጨናንቆ፤ ሕዝቡን በተለይም በአጠቃላይም ደረጃ እየበደለው መሆኑ የሚካድ አይደለም ። የኦሮሞ ሕዝብ ለመብቱ የሚያደርገው ትግል የሚደገፍና ፍትሐዊ ነው ብሎም ኢሕአፓ ሁሌም ከጎኑ ቆሟል ። አሁንም የተለወጠ የለም--ሕዝብና ቡድኖች፤ ድርጅቶች አንድ አይደሉምና ።

በልዩ ልዩ ከተሞች እየተካሄደ ያለው ትግል የአዲስ አበባ መስፋፋት ዕቅድ በሚለው ዙሪያ ቢለኮስም ዋናው አንቅሳቃሹ ግን ሕዝብ በወያኔ አገዛዝ ላይ ያለው ጥላቻና ተቃውሞ ነው ።ለዚህም ነው የአመጹ ይዘት ሰፋ ብሎና ብዙዎችንም እያቀፈ በመምጣት ላይ ያለው ።ለዚህም ነው ወያኔና መሰሎቹ አመጹን በአንድ አጥር ከተውና አካልለው ሌላው ገሸሽ እንዲል ለማድረግ እየጣሩ ያሉት ። ጊዜ የተፋቸው ጽንፈኞች አመቺ ሁኔታ ያገኙ መስሏቸውም ብቅ ብቅ ያሉትም ለዚህ ነው። ወያኔ በፀረ አማራ ቅስቀሳ ዙሪያ ስንቱን አሰልፎ፤ በሽግግሩ የበላይነቱን አስቀብሎ ፍጹም ስልጣንን ሊይዝ እንደቻለ ከ24 ዓመት በፊትም አይተናል ። ሶማሌ መጣብህ፤ እኛ ከሌለን ኦሮሞ ያርዳችኋል፤ ኢትዮጵያ ህልውናዋ ያከትማል ብሎ የሚለፍፈውን ጆሮ የሚሰጠው የለም ማለት አይቻልምና ወያኔ አሁንም ሕዝብን እርስ በርስ በሚያጣሉ በራሪ ወረቀቶች ሳይወሰን በድርጊትም ብዙ ክፍፍልና ፍጅት ሊያደርስ በመፍጨርጨር ላይ ነው ። ይህንን የከፍፍል እቅድ ይዘው በሌሎች ጭቁን ሕዝቦች ላይ ወንጀል የሚፈጽሙት ሁሉ ወደዱም ጠሉም ሰልፋቸው ከወያኔ ጋር ነው ።

ከዚህ ባሻገር ግን ይህን የአመፅ እንቅስቃሴ የጀመሩት ወጣቶች በተለይ ባለውለታ ናቸው ። የተሰዉትም ታሪክ የሚረሳቸው አይሆኑም ።አመጹ ሲፋፋም ሌሎችም መስዋዕት እንደሚሆኑ አንጠራጠርም ። በትግል መሰዋት ሁሌም ክቡር ነው ። ጭቆናን መቻልና በዝምታ መቀበል ነው መዋረድ። በመሆኑም አመጹ ይፋፋም ዘንድ ኢሕአፓ ጥሪውን እያስተጋባ አባላቱ በሞላ በአመቺው መንገድ በትግሉ ተሳታፊ እንዲሆኑም መልዕክቱን አስተላልፏል ። አሁን የሚጠበቀው ትግሉን ማስፋፋትና ሁሉንም ሕዝብ፤ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እንዲያቅፍ ማድረግ ነው። ከውሱን ጥያቄ ወደ ሰፊው አገር አቀፍ ጥያቄ እንዲያድግ ማድረግ ነው። አድማ፤አድማ አድማ፤ የማይቋረጥ አመጽ ። ለላ አማራጭ የለም ። መሬቱን መብቱን የተቀማ ዜጋ ከ94 ሚሊዮን አያንስም ። እስካሁን ድረስ ተጠቅቶ የቆየው ግን ወያኔ በአሰራጨው ከፋፋይና ዘረኛ መርዝ ነው ።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ቀደም ብሎ ተማሪዎች ጎጥና ብሔረሰብ ሳይለዩ ታግለው የካቲት 66ን አዋልደው ነበር ። ወያኔን በዚህ መልክ ማስወገድ ዛሬም ይቻላል ። መተባባርና ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መቆም ግን ቀዳሚ መሆን አለበት ። ትግል ድርጅትና ውስጣዊ ጥንካሬ ካጣ፤ ተቃውሞው ከተከፋፋለ፤ ግቡ ከተምታታ፤ አንዱ ሲጠቃ ሌላው በዝምታ ከቆመ ወያኔ አሸናፊ ይሆናል ። ተባብረን ኢትዮጵያን ከወያኔ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት ከሰሜን እስከ ደቡብ፤በመሀልም፤ በምስራቅና ምዕራብም ከተነሳን ግን የወያኔ ውድቀት ፈጣን ይሆናል ። የወያኔ የአፋኝ መሳሪያዎችም እንዲላሉና እምቢታን እንዲያሰሙ ማድረግም ይቻላል ። ወያኔ ለሥልጣኑ ሲል ጨካኝ እንደሚሆን የታየና እየታየ ያለም ነውና ተቃዋሚዎች ሕዝብ አስጨረሳችሁ እንባላለን በሚል ሳይሸማቀቁ ትግሉ ለሚጠይቀው መስዋዕትነት መዘጋጀትና ሕዝብንም ማስነሳት መከተልም ይገባቸዋል ።

ድርጅቶች በጸረ ወያኔ መርሃ ግብር ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመስረት እንድንተባበርም ኢሕአፓ ዳግም ጥሪውን ያስተላልፋል ።

አመጹ ይስፋፋ፤ሁሉም ዜጋ ይነሳ!
ድል በቆራጥ ትግል !!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France